# የምርምር ርእሶች

መምህሩ “ተማሪው ሊጽፍበት ይችላል” ብሎ የሚያስባቸውን የተለያዩ የምርምር ርእሶች ሊያቀርብለት ይችላል። ለናሙና ያህል የተወሰኑ ርእሶች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

| | ርእሶች |
|---|---|
| | |
| (ሀ) | **የስም አወጣጥ ሥርዓት**<br>• ተማሪው የቤተሰቡን አባላት፣ የቅርብና የሩቅ ዘመዶቹን ስሞች ያሰባስባል። ከዚያም እያንዳንዱ ስም ለምን እንደተሰጠ የቤተሰቡን አባላት በተለይም አባቱንና እናቱን እንደዚሁም ዘመዶቹን በመጠየቅ ይጽፋል።<br>• ኢትዮጵያ እያለ እሱ፣ ወንድሞቹ፣ እኅቶቹ ወይም ጓደኞቹ የቁልምጫ ስም ነበራቸው? ከነበራቸው ስሞቹን ይመዝግብና ለምን እነዚህ ስሞች እንደተሰጡ ምክንያቱን ይዘረዝራል።<br>• እስራኤል ከገባ በኋላ የዕብራይስጥ ስም አለው ወይ የለውም? ካለው ያንን ስም እንዴት መረጠ/እንዴት ተመረጠለት?<br>• እስራኤል ከገባ በኋላ የቤተሰብ ስሙ ማን ነው? |
| | |
| (ለ) | **ተማሪው ወይም ቤተሰቡ ወደ እስራኤል ያደረገው “ዓልያ” ታሪክ**<br>• የልጅነት ጊዜ ትዝታዎች<br>• በጐንደር ወይም አ.አበባ ካምፖች ያሉ ውጣ ውረዶች<br>• እስራኤል መቼ እንደገባና ሲገባ የነበረው ስሜት |
| | |
| (ሐ) | **የድኅረ “ዓልያ” ትዝታዎችና የተለያዩ የውኅደት ተግዳሮቶች**<br>• በመርካዝ ቅሊጣዎችና መኖሪያ ቤቶች አካባቢ<br>• በትምህርት ቤት<br>• በሥራ ቦታ |

| | |
|---|---|
| | |
| (መ) | የኢትዮጵያውያን ይሁዲዎች ሠርግ ሥነ ሥርዓት በኢትዮጵያና በእስራኤል በንጽጽር መልክ ሲታይ |
| | |
| (ሠ) | የኢትዮጵያውያን ይሁዲዎች የለቅሶ ሥነ ሥርዓት በኢትዮጵያና በእስራኤል በንጽጽር መልክ ሲታይ |
| | |
| (ረ) | ከኢትዮጵያውያን ይሁዲዎች የሃይማኖት በዓላት ውስጥ አንዱን በመውሰድ ዘርዘር ያለ ጽሑፍ ማዘጋጀት |
| | |
| (ሰ) | የኢትዮጵያውያን ይሁዲዎች ስኬት ምሳሌዎች በእስራኤል<br>• ተማሪው "ስኬት ላይ ደርሷል" የሚለውን ግለሰብ በግንባር ካልሆነም በስልክ በማነጋገር ጥሩ የምርምር ሥራ ሊያዘጋጅ ይችላል። |
| | |
| (ሸ) | አንዱ የምርምር ርእስ ሊሆን የሚችለው ወቅታዊ ጉዳዮች ወይም *actualia* የሚባለው ነው። |
| | |
| (ቀ) | አገሩ የዲሞክራሲ እንደመሆኑ መጠን ተማሪው የራሱን ርእስ በመምረጥም ምርምር ማድረግ ይችላል። |
| | |

እያንዳንዱ የምርምር ሥራ የሚከተሉትን ማካተት አለበት። የምርምሩ ርእስ፣ ተማሪው ያንን ርእስ ለምን እንደመረጠው አጭር ማብራሪያ፣ የምስጋና ገጽ (acknowledgment) ፣ የምርምሩ መግቢያ፣ የምርምሩ ዋና አካል፣ የምርምሩ መደምደሚያ፣ የመረጃ ምንጮች ዝርዝር bibliography (ቢያንስ ከ4 እስከ 6 መጻሕፍት ወይም ሌሎች ምንጮች)።